በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

# - ክፍል ፪


## መምህር፡-   ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

*ቦታ፦* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን  አዳራሽ

በየሳምንቱ  ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ነሐሴ ፳፪ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# <u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ</u>

## 6. <u>ክርስቲያናዊ ምክሮችን መቀበል ወይም መከተል</u>

- የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅበት አንዱ መንገድ የንስሐ አባታችንን፣ የወላጆችን፣ የቀሳውስትን፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን፣ የእግዚአብሔር ሰዎችን፣ የክርስቲያን ባልንጀሮቻችንን ምክር በመጠየቅና በመጠቀም ነው፡፡ ‹‹ በመልካምም ምክር ሰልፍ አድርግ። ›› <u>*ምሳ 20:18፡፡*</u> እንዳለ ጠቢቡ ሰሎሞን፡፡
- እንዲህ ዓይነት ምክሮችን ስንፈልግ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከተለያዩ ሰዎች በአንድ አቅጣጫ የጸናት ምክር ሆና ወደ እኛ ትደርሳለች፡፡ ‹‹በመካሮች ብዛት ግን ደኅንነት ይሆናል።›› እንዳለ <u>*ምሳ 11:14፡፡*</u>
- በሕይወታችን ውሳኔ የሚሹ ከበድ ያሉ ጉዳዮች ሲገጥሙን ከላይ እንደጠቀሰው የተለያዩ ክርስቲያኖችን ማማከር እንደ በጎ ነገር የሚቆጠር ነው፡፡ ‹‹ድልም ብዙ ምክር ባለበት ዘንድ ነው።›› <u>*ምሳ 24:6፡፡*</u>
- ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ በርካታ ሰዎች ‹‹የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል...።›› <u>*ካል ጢሞ 3:5-8*</u> ስላለን በሕይወታችን ጉዳይ የምናማክራቸውን ሰዎች በተመለከተ ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡ ሐዋርያው እንዲህ ያሉ ሐሰተኞች መምህራንን አስመልክቶ ደጋግሞ አስጠንቅቆናል፡፡
- ‹‹በክፉዎች ምክር ያልሄደ ምስጉን ነው...፡፡›› <u>*መዝ 1:1-2*</u>፣ ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ርጉም ነው...።›› <u>*ኤር 17:5-10*</u>፡ መልካም ክርስቲያን (ኦርቶዶክሳዊ) አማካሪ ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ... ይላል፡፡›› እያለ ወደ እግዚአብሔር የሚመራን ሲሆን ነፍሳችንም ‹‹እንዲሁ ነፍስ በወዳጁ ምክር ደስ ይላታል።›› <u>*ምሳ 27:9*</u> እንዳለ በርሱ ምክር ነፍሳችን ደስ ይላታል፡፡
- እጮኝነትን፣ ትዳርን፣ መቀጣጠርን፣ ንጽሕናን፣ የሥራ መስካችንን፣ የመኖሪያ አድራሻችንን፣ የምንማርበትን ት/ቤት መምረጥን፣ ልጆቻችንን፣ ጓደኛ መምረጥን፣ ከወላጆቻችን ጋር የሚኖሩንን ግኑኙነቶች፣ አገልግሎትን፣ የቤተ ክርስቲያንን ዶግማ በተመለከቱ ጉዳዮች ታላቅ ክርስቲያናዊ ምክር መጠየቅ ይጠበቅብናል፡፡
- የመልካም አማካሪ ምሳሌዎችም ቅዱስ ጳውሎስና፣ ጢሞቴዎስ፣ ቅዱስ እንጦንስና ቅዱስ አትናቴዎስ ናቸው፡፡
- <u>*በሐዋ 15*</u> የተጻፈው የሐዋርያት የመጀመሪያው ሲኖዶስም በቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ምክሮች ጥሩ ማሳያ ነው፡፡

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

## 7. የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ በመስማት

- እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ፈቃዱ ምን እንደሆነ በመንፈስ ቅዱስ ይናገራል ሲናገረንም ነበር፡፡ ለመስማት ፈቃደኞች ከሆን ድምጹን እንሰማለን፡፡
- በሰላም እየኖርን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የመፈጸም ፈቃደኝነቱ ካለን የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ እየሰማን ነው ማለት ነው፤ ይህም ድምጽ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመከራ ውስጥም ሆነን እስክናደርገው ድረስ የምንሰማው ሰላማዊ ድምጽ ነው፡፡
- ‹‹ጌታም የጭንቀትን እንጀራና የመከራን ውኃ ቢሰጥህም አስተማሪህ እንግዲህ ከአንተ አይሰወርም ዓይኖችህ ግን አስተማሪህን ያያሉ፥ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ ብትል ጆሮችህ በኋላህ። መንገዱ ይህች ናት በእርስዋም ሂድ የሚለውን ቃል ይሰማሉ።›› ***ኢሳ 30፡20-21፡፡***
- ሰላም እንዲሰማን የሚያድረገን፣ አንዳንዴም ባደረግነው መወቀስ እንዲሰማን የሚያደርገን ድምጽ የመንፈስ ቅዱስ ድምጽ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው እግዚአብሔር በምድር መናወጥ፣ በእሳት ወይም በመሳሰለው መንገድ ሳይሆን በትንሽ የዝምታ ድምጽ እንደሚናገረን እንረዳለን፡፡ ‹‹ እርሱም፦ ውጣ፥ በተራራውም ላይ በእግዚአብሔር ፊት ቁም አለ። እነሆም፥ እግዚአብሔር አለፈ፥ በእግዚአብሔርም ፊት ትልቅና ብርቱ ነፋስ ተራሮቹን ሰነጠቀ ዓለቶቹንም ሰባበረ፥ እግዚአብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም። ከነፋሱም በኋላ የምድር መናወጥ ሆነ፥ እግዚአብሔር ግን በምድር መናወጥ ውስጥ አልነበረም። ከምድር መናወጥ በኋላ እሳት ሆነ፥ እግዚአብሔር ግን በእሳቱ ውስጥ አልነበረም። ከእሳቱም በኋላ ትንሽ የዝምታ ድምፅ ሆነ።›› ***ቀዳ ነገ 19፡11-12፡፡***

## 8. እግዚአብሔርን በትዕግሥትና በተስፋ በመጠበቅ

- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ትዕግሥት ቁልፍ ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔር በኛ ትዕግሥት እንደሚያደርግ እኛም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመመርመርና ለማወቅ ትዕግሥተኞች መሆን ይጠበቅብናል፡፡
- ትዕግሥት ወደ ድምዳሜ ከመዝለል፣ ድንገተኛ፣ ስሜታዊና ፍትሕ የጎደለበት ውሳኔ ከመወሰን መቆጠብን ትሻለች፡፡ በዚህ አቅጣጫ የሚወሰኑ ውሳኔዎችም ፈጽመው የእግዚአብሔር ፈቃድ ያለባቸው አይደሉም፡፡

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

## 8. እግዚአብሔርን በትዕግሥትና በተስፋ በመጠበቅ…

- ‹‹ክፉ እመልሳለሁ አትበል እግዚአብሔርን ተማመን፥ እርሱም ያድንሃል።›› ***ምሳ 20:22*** ‹‹በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፥ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል። መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ፥ በእርሱም ታመን፥ እርሱም ያደርግልሃል። ጽድቅህን እንደ ብርሃን፥ ፍርድህንም እንደ ቀትር ያመጣል። ለእግዚአብሔር ተገዛ ተስፋም አድርገው። መንገድም በቀናችለትና ጥመትን በሚያደርግ ሰው አትቅና።›› ***መዝ 36(37):4-7፡፡***
- **እግዚአብሔር እኛን፣ ችግራችንንና ትግላችንን ሁሉ ፈጽሞ አይረሳም፤ ፈጽሞ ያስበናል ያስብልናል እንጂ፡፡** ‹‹በውኑ ሴት ከማኅፀንዋ ለተወለደው ልጅ እስከማትራራ ድረስ ሕፃንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን? አዎን፥ እርስዋ ትረሳ ይሆናል፥ እኔ ግን አልረሳሽም። እነሆ፥ እኔ በእጄ መዳፍ ቀርጬሻለሁ፥ ቅጥሮችሽም ሁልጊዜ በፊቴ አሉ።›› ***ኢሳ 49:15-16*** **እንዳለን፡፡**
- ***በራእ 14:12*** ‹‹የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁት ኢየሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትዕግሥታቸው በዚህ ነው።›› **የሚለው ቃልም አውሬውንና ምልክቱንም ድል የሚያደርጉ ምልክት እንዳላቸውና ምልክታቸውም ትዕግሥት እንደሆነ የሚያስረዳን ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ይፈጽማሉ አምላካችን መድኃኔዓለምንም በተስፋ ይጠባበቁታል፡፡**

## 9. እግዚአብሔር በሕይወታችን በሮችን እንደሚከፍትና እንደሚዘጋ በመገንዘብ

- **የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅበት አንድ ቀላል መንገድ በሚከፍትልንና በሚዘጋብን በር የምንማረው ትምህርት ነው፡፡ ሁላችንም የተዘጋውም ሆነ የተከፈተልን በር ልምዶች አሉን፤ ይህም እግዚአብሔር በቀላሉ ፈቃዱን ለእኛ የሚያሳውቅበት መንገድ ነው፡፡**
- **ባለፉት ጊዜያት ከነበሩን ልምዶች የትኛው በር እንደተዘጋ የቱ እንደተከፈተ መመርመራችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ የበለተ ለመረዳት ዕድል ይሰጠናል፡፡ በሕይወት ከገጠሙን ችግሮች ወይም በቀላሉ ከተሳኩልን ጉዳዮች ትምህርት መውሰድ ይኖርብናል፡፡**

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

## 9. እግዚአብሔር በሕይወታችን በሮችን እንደሚከፍትና እንደሚዘጋ በመገንዘብ…

- እግዚአብሔር ፈቃዱን እንድናደርግ ደጆቹን ሲከፍትልን ፈቃዱ ሰላምን፣ ደስታን፣ መጠበቅን/ደኅንነትን፣ በእግዚአብሔር መተማመንን፣ ምንም ዓይነት ግጭትና እንቅፋት እንኳ ቢኖር በድል የምናጠናቅቅበት ዕድል አብሮት ይገኛል፡፡
- እግዚአብሔር በሮቹን ሲዘጋ ግጭት፣ እንቅፋት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ የሰላም መታጣት፣ መገለል፣ ኢፍትሐዊነት፣ ሐዘንና፣ ተስፋ መቁረጥ ይከቡናል፡፡
- በሮቹ ሲዘጉብን ነገሮች የበለጠ የከፉ እንዳይሆኑ ወደ ጠበኝነት/ግጭት ማምራት የለብንም፤ በሩ ክፍት ሆኖ ሲሰጠንም በሌላ በኩል ስላለው ሁኔታ ሳንጨነቅና ሳንፈራም ወደ ውስጥ ዘልቀን እንግባ፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ በሕይወታችን ስለተከፈተልንና ስለተዘጋውም በር እንድናስብ መልእክት ጽፎልናል፡፡ ‹‹ስለ ክርስቶስም ወንጌል ወደ ጢሮአዳ በመጣሁ ጊዜ፥ ለጌታ ሥራ በር ምንም ቢከፈትልኝ፥ ቲቶን ወንድሜን ስላላገኘሁት መንፈሴ ዕረፍት አልነበረውም፥›› ***2ኛ ቆሮ 2፡12፡፡***
- በሮቹ ሲከፈቱልንም በበሩ ሌላኛው በኩል ያለው ምንም ይሁን ምን መጨነቅ የለብንም፤ ይመራን ዘንድ ዓይናችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አድርገን ወደፊት ስንራመድ ቃሉም እንደማንተላለፍ በማስተዋል ሆነን እንንዝ፡፡
- ‹‹ እግዚአብሔር ለቀባሁት፥ አሕዛብንም በፊቱ አስገዛ ዘንድ የነገሥታትንም ወገብ እፈታ ዘንድ፥ በሮቹም እንዳይዘጉ መዝጊያዎቹን በፊቱ እከፍት ዘንድ፥ ቀኝ እጁን ለያዝሁት ለቂሮስ እንዲህ ይላል። በፊትህ እሄዳለሁ ተራሮችንም ትክክል አደርጋለሁ፥ የናሱንም ደጆች እሰብራለሁ የብረቱንም መወርወሪያዎች እቈርጣለሁ በስምህም የምጠራህ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እኔ እንደ ሆንሁ ታውቅ ዘንድ በጨለማ የነበረችውን መዝገብ በስውርም የተደበቀችውን ሀብት እሰጥሃለሁ።›› ***ኢሳ 45፡1-3፡፡*** እንዳለ ፈቃዱን ያደርግ ዘንድ ደጆቹን ሲከፍትልን በሮቹን ይሰባብራቸዋል የብረት መወርወሪያዎችንም ዳግመኛ እንዳይዘጉብን ይቆርጣቸዋል፡፡

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

9. **እግዚአብሔር በሕይወታችን በሮችን እንደሚከፍትና እንደሚዘጋ በመገንዘብ…**

- በመጽሐፍ ቅዱሳችን እግዚአብሔር በሮችን በመክፈትና በመዝጋት ሥራውን ይሠራ እንደነበር እናነባለን፡-
  - ዮናስ፡- ለእግዚአብሔር አልታዘዝ ባለ ጊዜ ወደ ጠርሴስ የነበረው በር ተዘግቶበታል፤ ንስሐ ሲገባና ሲመለስ ግን የነነዌ በር ተከፍቶለታል፡፡
  - በለዓም፡- አልታዘዝ ባለ ጊዜ ደጆቹ ተዘግተውበታል፡፡ ‹‹እርሱም ስለ ሄደ እግዚአብሔር ተቈጣ የእግዚአብሔርም መልአክ ሊቋቋመው በመንገድ ላይ ቆመ፡፡›› ***ዘኍ 22፡22፡፡***
  - ሳውል፡- ወደ ደማስቆ ሲሄድ ሳለ ኢየሱስ ክርስቶስ በሮቹን ዘጋበት፤ ሳውልም ይህ የተዘጋ በር ሕይወቱን ለውጦታል፡፡
  - ሙሴ፡- ሙሴና እስራኤላውያን ግብጽን ለቀው እንዲወጡ በሮቹን ከፍቶላቸዋል፡፡
  - ቅዱስ ጴጥሮስ፡- ክዶት የነበረ ቢሆንም ንስሐውን ተቀብሎ ***በዮሐ 21*** እንደታፈልን በሮቹን ከፍቶለት በጎችን፣ ጠቦቶች፣! ግልገሎችን ለመጠበቅ ፈቅዶለታል፡፡
- እግዚአብሔር በሮችን በመዝጋትና በመክፈት ሰዎች ፈቃዱንእንዲያደርጉ የተጠቀመበት መንገድ ልቦናቸውን በመመለስ ነው፡፡ ልብን መመለስ እግዚአብሔር ፈቃዱን ለማድረግ የተጠቀበት መሣሪያ ነው፡፡
  - እግዚአብሔር የፈርዖን አደንድኖ በመጨረሻ ክብሩን በመግለጥ እስራኤልን ነጻ አውጥቶአቸዋል፡፡
  - በዕለተ ሆሳዕና ጌታችን በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች እንደ ንጉሥ ያከበሩት ቢሆንም ከጥቂት ቆይታ በኋላ ግን እንደ ወንጀለኛና በደለኛ ቆጥረውታል፡፡

# <u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ</u>

## 9. <u>እግዚአብሔር በሕይወታችን በሮችን እንደሚከፍትና እንደሚዘጋ በመገንዘብ…</u>

- **እግዚአብሔር ልብን እንደሚቆጣጠር ኪሚያሳዩን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል፡-**
  - ‹‹እንዲሁም። ዓይኖቻቸው እንዳያዩ ጆሮቻቸውም እንዳይሰሙ እግዚአብሔር የእንቅልፍ መንፈስን እስከ ዛሬ ድረስ ሰጣቸው ተብሎ ተጽፎአል።›› ***<u>ሮሜ 11፡8</u>***
  - ‹‹እንዲህም አላቸው፡- ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤ በውጭ ላሉት ግን፥ አይተው እንዲያዩ እንዳይመለከቱም፥ ሰምተውም እንዲሰሙ እንዳያስተውሉም፥ እንዳይመለሱ ኃጢአታቸውም እንዳይሰረይላቸው ነገር ሁሉ በምሳሌ ይሆንባቸዋል።›› ***<u>ማር 4፡11-12።</u>***
  - ‹‹ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል። ›› ***<u>ካል ተሰ 2፡10-11</u>***
  - ‹‹እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፡- ወደ ግብፅ ስትመለስ በእጅህ ያደረግሁትን ተአምራት ሁሉ በፈርዖን ፊት ታደርገው ዘንድ ተመልከት እኔ ግን ልቡን አጸናዋለሁ፥ ሕዝቡንም አይለቅቅም። ›› ***<u>ዘጸ 4፡21</u>*** **እንዳለ** ***<u>በዘጸ 7፡7፣ 9፡12፣ 10፡1፣ 11፡10፣14፡4።</u>*** **የፈርዖንን ልብ መደንደን እናነባለን።**
  - ‹‹ፈርዖንም በዚህ ጊዜ ደግሞ ልቡን አደነደነ፥ ሕዝቡንም አልለቀቀም።›› ***<u>ዘጸ 8፡32።</u>***
  - ‹‹እነሆም እኔ የግብፃውያንን ልብ አጸናለሁ፥ በኋላቸውም ይገባሉ በፈርዖንና በሠራዊቱም ሁሉ በሰረገሎቹም በፈረሰኞቹም ላይ ክብር አገኛለሁ። ›› ***<u>ዘጸ 14፡17።</u>***
  - ‹‹የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎን ግን ያሳልፈን ዘንድ አልፈቀደም እንደ ዛሬው ሁሉ በእጅህ አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ አምላክህ እግዚአብሔር መንፈሱን አደንድኖታልና፥ ልቡንም አጽንቶታልና።›› ***<u>ዘዳግ 2፡30።</u>***
  - ‹‹የኤዶምያስንም አማልክት ስለ ፈለጉ በጠላቶቻቸው እጅ አሳልፎ ይሰጣቸው ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበረና አሜስያስ አልሰማም።›› ***<u>ካል ዜና 25፡20።</u>***

# <u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ</u>

9. **<u>እግዚአብሔር በሕይወታችን በሮችን እንደሚከፍትና እንደሚዘጋ በመገንዘብ…</u>**

- **እግዚአብሔር ልብን እንደሚቆጣጠር ኪሚያሳዩን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል፡-**
  - ‹‹በዓይናቸው እንዳያዩ፥ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ ተመልሰውም እንዳይፈወሱ፥ የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን፥ ጆሮአቸውንም አደንቍር፥ ዓይናቸውንም ጨፍን አለኝ። ›› ***<u>ኢሳ 6፡10፡፡</u>***
  - ‹‹ትዋረጂማለሽ፥ በመሬትም ላይ ሆነሽ ትናገሪያለሽ፥ ቃልሽም ዝቅ ብሎ ከአፈር ይወጣል ድምፅሽም ከመሬት እንደሚወጣ እንደ መናፍስት ጠሪ ድምፅ ይሆናል፥ ቃልሽም ከአፈር ወጥቶ ይጮኻል።›› ***<u>ዘዳግ 29፡4፡፡</u>***
  - ‹‹ማንም ሰው ከእስራኤል ልጆች ከወንድሞቹ አንዱን ሰርቆ እንደ ባሪያ ሲያደርግበት ወይም ሲሸጠው ቢገኝ፥ ያ ሌባ ይሙት እንዲሁም ክፉውን ነገር ከመካከልህ ታስወግዳለህ።›› ***<u>ኤር 24፡7፡፡</u>***
  - ‹‹ከሳሙኤልም ዘንድ ለመሄድ ፊቱን በመለሰ ጊዜ እግዚአብሔር ሌላ ልብ ለወጠለት በዚያም ቀን እነዚህ ምልክቶች ሁሉ ደረሱለት።›› ***<u>ቀዳ ሳሙ 10፡9፡፡</u>***
  - **ሰይጣን ራሱ የዕድልን በር ስለሚከፍትና ስለሚዘጋ በ‹‹መክፈትና በመዝጋት›› ጉዳይ መጠንቀቅ አለብን፡፡** ‹‹ ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና።›› ***<u>ካል ቆሮ 11፡14፡፡</u>***
  - **በራሳችን ፍላጎትና ፈቃድ እንዲከፈትልንና እንዲዘጋልንም ሁኔታዎችን የምንቀምምና የምናመቻች እንዳንሆንም መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡**

# <u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ</u>

10. <u>**ውሳኔ ወስነን ተግባራዊ በማድረግ**</u>

- **በነዚህ ሁሉ ሂደቶች ውስጥ ካለፍን በኂላ እግዚአብሔር ከኛ ጋር እንደሆነ በመተማመን በእግዚአብሔር ወደፊት መራመድ አለብን፡፡** ‹‹በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም ከሙሴ ጋር እንደ ሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ አልጥልህም፥ አልተውህም።ለአባቶቻቸው። እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልሁላቸውን ምድር ለዚህ ሕዝብ ታወርሳለህና ጽና፥ አይዞህ። ›› <u>***ኢያ 1፡5-6፡፡***</u>
- **አሁን እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ተከትለነዋል፣ እርሱም ፈቃዱን እንፈጽምለት ዘንድ ሕያዋን አድርጎናልና እንደ ኢያሱ ተነስተን** ‹‹የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ምድርን እሰልል ዘንድ ከቃዴስ በርኔ በላከኝ ጊዜ እኔ የአርባ ዓመት ሰው ነበርሁ እኔም በልቤ የነበረውን ቃል መለስሁለት። ከእኔ ጋር የወጡ ወንድሞቼ ግን የሕዝቡን ልብ አቀለጡ እኔ ግን አምላኬን እግዚአብሔርን ፈጽሜ ተከተልሁ። ሙሴም በዚያ ቀን፡- አምላኬን እግዚአብሔርን ፈጽመህ ተከትለሃልና እግርህ የረገጠው ምድር ለአንተና ለልጆችህ ለዘላለም በእርግጥ ርስት ይሆናል ብሎ ማለ። አሁንም፥ እነሆ፥ እግዚአብሔር ለሙሴ ይህን ቃል ከተናገረ በኋላ፥ እስራኤል በምድረ በዳ ሲዞሩ፥ እርሱ እንደ ተናገረኝ እግዚአብሔር እነዚህን አርባ አምስት ዓመት በሕይወት አኖረኝ አሁንም፥ እነሆ፥ ለእኔ ዛሬ ሰማንያ አምስት ዓመት ሆነኝ። ሙሴም በላከኝ ጊዜ እንደ ነበርሁ፥ ዛሬ ጕልበታም ነኝ ጕልበቴም በዚያን ጊዜ እንደ ነበረ፥ እንዲሁ ዛሬ ለመዋጋት ለመውጣትም ለመግባትም ጕልበቴ ያው ነው። አሁን እንግዲህ በዚያን ቀን እግዚአብሔር የተናገረውን ይህን ተራራማ አገር ስጠኝ አንተ በዚያ ቀን ዔናቃውያን ታላላቆችና የተመሸጉ ከተሞችም በዚያ እንዳሉ ሰምተህ ነበር ምናልባት እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ይሆናል፥ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረኝ አሳድዳቸዋለሁ።›› <u>***ኢያ 14፡9-12፡፡***</u> **እንበል፡፡**

ወስብሐት ለእግዚአብሔር”፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org